# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# ህብረት ሥራ ኤጀንሲ

## የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ

## በውክልና ለማስመርመር

## የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 100/2014

መጋቢት2011 ዓ/ም

ማውጫ ገጽ

1. መግቢያ ........ 3

ጠቅላላ ........ 4

አንቀጽ 1፣ አጭር ርዕስ ........ 4

አንቀጽ 2፣ ትርጓሜ ........ 4

አንቀጽ 3፣ የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን፣ ........ 5

አንቀጽ 4፡- የመመሪያው ዓላማ ........ 5

ክፍል ሁለት ........ 5

ስለ ተወካይ ሂሳብ መርማሪ አቋምና የሥራ ስምሪት ........ 5

አንቀጽ 5፡ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች ........ 5

አንቀጽ 6፣ ስለተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ሥነ ምግባር፣ ........ 6

አንቀጽ 7፣ የራሱን ጥቅም ስለመሻት፣ ........ 7

አንቀጽ 8፣ ከቡድን አባላት ውስጥ የራሱን ሥራ ኦዲት ማድረግ አለመቻል፡፡ ........ 7

አንቀጽ 9፣ ከኦዲት ተደራጊ አካላት ጋር የጥቅም ግንኙነትና ዝምድና አለመኖር፣ ........ 7

አንቀጽ 10፣ በሂሣብ ምርመራው አግባብ ያለው ባለሥልጣን ተግባር እና ሃላፊነት ........ 8

አንቀጽ 11፣ የተወካይ ሂሳብ መርማሪዎችን ዝርዝር ስለመያዝ ........ 8

አንቀጽ 12፣ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎችን ስለመምረጥ፣ ስለመመደብና ስለማንሳት ........ 9

ክፍል ሦስት ........ 10

ለሂሳብ ምርመራው ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና ሌሎች ተግባራት ........ 10

1.1 አንቀጽ 13፣ በኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት መደረግ ስለሚገባው ቅድመ ዝግጅት 10

1.2 አንቀጽ 14፣ ተወካይ ሂሣብ መርማሪዎች በሥራቸው ወቅት ትኩረት ሊያደርጉባቸው ስለሚገቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጾች እና ሌሎች ነጥቦች፤ ........ 11

አንቀጽ 15፣ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሲመረምሩ ማከናወን ስለሚገባቸው ዝርዝር ተግባራት፣ ........ 12

15.1 በሥራ አመራር ኦዲት ትኩረት የሚሰጥባቸው፣ ........ 12

በፋይናንስ ኦዲት ትኩረት የሚሰጥባቸው፣ ........ 13

የንብረት ቁጥጥር ኦዲት ትኩረት የሚሰጥባቸው፣ ........ 14

ክፍል አራት ............ 15

የኦዲት ሪፖርት ............ 15

አንቀጽ 16፤የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት አዘገጃጀት፤ ............ 15

አንቀጽ 17፤ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ስለሚቀርብበት ጊዜ ............ 15

አንቀጽ 18፤ ስለ ሂሳብ ምርመራ ሪፖርት አቀራረብ ............ 16

አንቀጽ 19፤ የሂሳብ መግለጫዎችና አባሪዎች ............ 16

ክፍል አምስት ............ 16

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ............ 16

አንቀጽ 20፤ ስለ ክትትልና ቁጥጥር ............ 16

አንቀጽ 21፤ መረጃን ስለመግለጽ ............ 17

አንቀጽ 22፤ ሥልጠና ስለመስጠት ............ 17

አንቀጽ 23፤ የኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት እና የኦዲት ተደራጊ አካላት ግዴታ እና ተጠያቂነት ............ 17

አንቀጽ 24፤ የተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ተጠያቂነት እና ኃላፊነት፤ ............ 17

አንቀጽ 26፤ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ............ 18

## 1. መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሺዎች የሚቆጠሩ ህብረት ሥራ ማኅበራት ሲኖሩ እነዚህም ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሰፊውን እና በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ኅብረተሰብ በማቀፍ ለከተማችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

ኅብረት ሥራ ማኅበራቱም አገልግሎት ሰጪ እንደመሆናቸው መጠን የሚያከናውኑት ተግባር በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እየተመዘነ አዋጭ እና ለአባላት ጠቀሜታ የሚሰጡ ተቋማት መሆናቸውን ለመለካት እንዲቻል እና ዘመናዊና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት እንዲከተሉ እንዲሁም በሌሎች ተቋማት ዘንድ አመኔታ ለማሳደር እንዲችሉ ማድረግ የከተማው ህብረት ስራ ኤጀንሲ ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አግባብ ያለው ባለሥልጣን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማንኛውንም ኅብረት ሥራ ማህበር ሂሣብ ራሱ ወይም እሱ በሚወክለው ሰው መመርመር እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በከተማችን ነባራዊ ሁኔታ የስራ ዕድል የሚፈጠርላቸው በርካታ ዜጎች በአማራጭነት በህብረት ስራ ማህበር የመደራጀት ፍላጎት በማሳየታቸው ፤ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በደረጃ፤ በአይነትና በቁጥር እያደጉ በመምጣታቸው ፤ የህዝብ ተቋማትም በሸማች ህብረት ስራ ማህበራት እንዲተዳደሩ በመደረጉ አስቀድሞ ይደረግ እንደነበረው አግባብ ባለው ባለሥልጣን ብቻ ይህን አገልግሎት ለማዳረስ አልተቻለም፡፡

ስለዚህ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሂሳብ በአዋጁ መሠረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መመርመር እንዲቻል በውክልና ማስመርመር የሚቻልበትን አሰራር መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 76 ቁጥር 3 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ በውክልና ለማስመርመር የሚያስችል ቁጥር 5/2010 መመሪያን አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ 1፣ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ህብረት ስራ ኤጀንሲ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ በውክልና ለማስመርመር የወጣ መመሪያ ቁጥር 100/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2፣ ትርጓሜ

በኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው ደንብ የተሰጡት ትርጉሞች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

**"ተወካይ ሂሳብ መርማሪ" ማለት፡-** በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 50 መሠረት አግባብ ያለው ባለስልጣን የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ እንዲመረምርለት ውክልና የሰጠው እና የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሳብ መመርመር የሚችሉ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ዝርዝር ውስጥ የመዘገበው ኦዲተር ወይም የኦዲት ድርጅት ወይም የኦዲት ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፡፡

**"የሂሳብ ምርመራው ቡድን አባላት" ማለት** ፡-ተወካዩ የኦዲት ድርጀት ወይም የኦዲት ኅብረት ሥራ ማኅበር ለሂሳብ ምርመራ ሥራው የሚያሰማራቸው እና የሚያስተዳድራቸው ሂሳብ መርማሪዎችን ነው፡፡

**ኦዲት ተደራጊ" ማለት** በዚህ መመሪያ መሠረት በተወካይ ሂሳብ መርማሪ ሂሳቡን በራሱ ወጪ የሚያስመረምር ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፡፡

**"ኦዲት ተደራጊ አካላት" ማለት** ሂሳቡ በሚመረመረው ኅብረት ሥራ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የሥራ አመራር አካላት እና የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ለማከናወን የተቀጠሩ ቅጥር ሠራተኞችን ነው፡፡

**"ሥራ መሪ" ማለት** ለኅብረት ሥራ ማህበር ሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪ የሆነና የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የተወሰኑ ሰዎችን ሥራ በመምራት በማስተባበር በመቆጣጠር የኅብረት ሥራ ማኅበር ሊወስድ የሚገባውን እርምጃ በተሰጠው ውክልና መሠረት የሚወስድ እና ከእሱ ውክልና በላይ የሆኑትን የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የሥራ ሃላፊ ነው፡፡

**"አዋጅ" ማለት** የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ነው፡፡

**"አግባብ ያለው ባለስልጣን" ማለት** በአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ እና በተዋረድ እስከ ወረዳ ያለው አደራጅ መስሪያ ቤት (አካላት) ነው፡፡

## አንቀጽ 3፣ የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን፣

ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተደራጁ እና በተመዘገቡ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 4፡- የመመሪያው ዓላማ

4.1 በአሁኑ ሰዓት በከተማችን ውስጥ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ደረጃቸው እና ቁጥራቸው እያደገ በመምጣቱ የማደራጀት እና የመቆጣጠር ሥልጣን በተሰጠው አካል ብቻ የሂሣብ ምርመራ ሥራውን ለማዳረስ ባለመቻሉ በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 50 በተደነገገው መሠረት ውክልና መስጠቱ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ በዓመት አንድ ጊዜ ለመመርመር የሚያስችል በመሆኑ፤

4.2 ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አንዳንድ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 በሚጻረር መልኩ በራሳቸው ፈቃድ እየተከተሉት ያለውን በሌሎች አካላት ሂሣባቸውን የማስመርመር ሂደት ስርዓት በያዘ መልኩ ሕግና ደንብን ተከትሎ እንዲከናወን ስለሚያስችል፣

4.3 የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሀብትና ንብረት ከምዝበራ እና ከብክነት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንዲሁም ጠንካራና ቀጣይነት ያላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራትን ለመፍጠር ስለሚያስችል፣

4.4 እንዲሁም ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች የንግድ ተቋማት የሚለዩበት የራሳቸው ባሕርይ ስላላቸው ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች እነኝህን የኅብረት ሥራ ማኅበራት ልዩ ባህርያት በመረዳት ሂሣባቸውን እንዲመረምሩ ስለሚያስችል ነው፡፡

4.5 የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለሁሉም ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተደራሽ ማድረግ ስለሚያስችል ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለ ተወካይ ሂሳብ መርማሪ አቋምና የሥራ ስምሪት

## አንቀጽ 5፡ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች

5.1 የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም እሱ ከሚወክለው አካል ሂሣብ ለመመርመር የሚያስችለውን የሙያ ፈቃድ ያገኘ እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ማቅረብ የሚችል

5.2 በአገሪቱ ሕግ መሠረት የኦዲት ሥራ ለመስራት የሚያስችል ወቅታዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያለው

5.3 የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሂሣብ ምርመራን በተመለከተ ከፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ወይም ከሌሎች ሕጋዊ አካላት ሥልጠና የወሰደ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ቢሆን ይመረጣል፡፡

5.4ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ወይም ከሂሳብ መርማሪው ቡድን አባላት ውስጥ ቢያንስ አንዱ ከዚህ በፊት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሳብ የመረመረ ቢሆን ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

5.5 የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሂሣብ ለመመርመር ብቁ ባለሙያዎችን በሥራ ላይ ማሰማራት የሚችል፣ ይህ ሣይሆን ቀርቶ ለሚከተለው ማንኛውም ኪሣራና ችግር አስቀድሞ ኃላፊነቱን የሚወስድ፣

5.6እንደ አስፈላጊነቱ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ 6፣ ስለተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ሥነ ምግባር፣

በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙ የኦዲተሮች የሥነ ምግባር መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ እና የአሰራር ሕጋዊነትን የሚያረጋግጡ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሂሳብ ምርመራ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ማክበርና በተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች የሙያ ነፃነት ላይ ከሚከሰቱ ስጋቶች ራሳቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል፡፡

በዚህም መሠረት፣

6.1የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ እንዲመረምር ውክልና የተሰጠው ማንኛውም ሂሳብ መርማሪ ሙያዊ ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ተአማኒነቱን፣ ሚዛናዊነቱን እና ገለልተኛነቱን ከሚያጓድል የጥቅም ግጭት መራቅ አለበት፣

6.2 በተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች የሙያ ነፃነት ላይ የሚከሰቱ የጥቅም ግጭት የሚያስከትሉ ስጋቶች የሚባሉት፣

6.2.1 የራስን ጥቅም መሻት፣

6.2.2 ከቡድን አባላት ውስጥ የራስን ሥራ ኦዲት ማድረግ፣

6.2.3 ከኦዲት ተደራጊ አካላት ጋር ጤናማ ያልሆነ የጠበቀ ግንኙነትና ትውውቅ እና ሌሎች መሰል የሙያ ነፃነትን ሊያጓድሉ የሚችሉ ስጋቶች ናቸው፡፡

6.3 በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት የኦዲት የሥነ ምግባር መርሆዎች የተወካዩን ሂሳብ መርማሪ የሥነ ምግባር ጉድለቶች በማይሸፍኑበት ጊዜ ፍቃድ በሰጠው አካል የወጡ የሥነ ምግባር ደንቦች እንዲሁም በኦዲት አሰራር የሚታወቁ እና ተቀባይነት ያገኙ አሰራሮች በሚሚያነት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 7፣ የራሱን ጥቅም ስለመሻት፣

**ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ በማንኛውም ምክንያት**

7.1 ከኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት ወይም ከኦዲት ተደራጊ አካላት ቀጥተኛ የሆነ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ማንኛውንም ሕገ ወጥ ጥቅም መቀበል ለኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኀበር ወይም ለኦዲት ተደራጊ አካላት የብድርም ሆነ የዋስትና አገልግሎት መስጠት ወይም ከእነሱ መቀበል የለበትም፡

7.2 ከኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት ጋር የጥቅም ግንኙነት መፍጠር የለበትም

7.3 የተወካዩን ሂሳብ መርማሪ ሪፖርት በሚጠቀሙ አካላት ዘንድ የተወካዩን ሂሳብ መርማሪ ሙያዊ አስተያየት ሊያዛቡ ወይም ሊቀንሱ የሚችሉ ሌሎች ሁኔታዎች መፍጠር፤ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 8፣ ከቡድን አባላት ውስጥ የራሱን ሥራ ኦዲት ማድረግ አለመቻል፡፡

የተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ወይም የሂሳብ ምርመራው ቡድን አባል የራሱን ሥራ ኦዲት ማድረግ የማይችለው፣

8.1 የኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኀበር የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቅጥር የሥራ መሪ የነበረ ከሆነ፣

8.2 የኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኀበር ተቀጣሪ ሠራተኛ ሆኖ በሠራተኛነቱ በኦዲት አገልግሎቱ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ፣

8.3 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ለኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኀበር ከኦዲት ውጭ በኦዲት ሥራው ላይ ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል የሂሳብ ሥራ እና ማንኛውም ሌላ አገልግሎት የሰጠ ከሆነ፣ወይም፣

8.4 ሌሉች የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ በሚችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ተሳትፎ ከሆነ፣ በማንኛውም መልኩ የኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራትን ሂሣብ ወይም የአሰራር ሕጋዊነት ማረጋገጥ አይችልም፡፡

### አንቀጽ 9፣ ከኦዲት ተደራጊ አካላት ጋር የጥቅም ግንኙነትና ዝምድና አለመኖር፣

ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ወይም የሂሳብ ምርመራው ቡድን አባል የጥቅም ግንኙነትና ዝምድና አለው የሚባለው፣

9.1ቤተሰብ ወይም የቅርብ ዘመድ በኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት ውስጥ ከኦዲት ሥራ አመራር ኮሚቴነት ወይም በቅጥር የሥራ መሪነት ወይም በሌላ የሚሰራ ከሆነ፣

9.2 ቤተሰብ ወይም የቅርብ ዘመድ በኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት ውስጥ ቅጥር ሠራተኛ ሲሆንና ያለው የሥራ መደብ በኦዲት ሥራው ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ፣

9.3 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ የተመርማሪ ኀብረት ሥራ ማኀበር አባል ከሆነ፤

9.4ከኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት የሥራ አመራር ኮሚቴዎች ወይም ቅጥር የሥራ መሪዎች ጋር ሌሎች ተመሳሳይ ግንኙነትና ትውውቅ ያላቸው ከሆነ በማንኛውም ምክንያት የኦዲት ተደራጊ ማህበራትን ሂሣብ መመርመር ወይም የአሰራር ሕጋዊነት ማረጋገጥ አይችልም፣

**አንቀጽ 10፣ በሂሣብ ምርመራው አግባብ ያለው ባለሥልጣን ተግባር እና ሃላፊነት**

10.1 በየአመቱ በተወካይ ሂሳብ መረማሪዎች ሂሳባቸውን ማስመርመር የሚችሉ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሚለይበት መመዘኛ መስፈርት ያወጣል፤

10.2 በወጣው መስፈርት ሂሳባቸውን በተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ማስመርመር የሚችሉ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በመለየት ሂሳባቸውን በተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች እንዲያስመረምሩ ለኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በበጀት አመቱ መጀመሪያ ያሳውቃል፤ ሂሳባቸውንም በየአመቱ የማያስመረምሩ መሆኑን ይከታተላል፡፡

10.3 ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሂሳባቸውን የማስመርመር ጥያቄ ሲያቀርቡ ጥያቄያቸውን መርምሮ በአንድ ቀን ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡

10.4 የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ ለመመርመር የሚቀርቡ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን እና አግባብ ባለው ባለስልጣን የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ የሚመረምሩ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ዝርዝር ውስጥ መመዝገባቸው በማጣራት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

10.5 ከተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ጋር ለሚፈጸመው የሥራ ውል ሙያዊ እገዛ ይሰጣል፡፡

10.6 ለተወካይ ሒሣብ መርማሪዎች ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ምንነት እና ሂሳብ አያያዝ ሥልጠና ይሰጣል፡፡

10.7 ለኦዲቱ ሥራ መሳካት አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይኖርበታል፤

10.8 ተወካይ ሂሳብ መርማሪ ያዘጋጀው የኦዲት ሪፖርት ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ቀርቦ ከማስወሰኑ በፊት አግባብ ያለው ባለስልጣን ይገመግማል፤ ተቀባይነት ያለው ለመሆኑ አስተያየት ይሰጣል፤

10.9 የኦዲት ሪፖርቱን ከመርማሪው ጋር በመሆን ለህብረት ሥራ ማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ያስወስናል፤ በኦዲት ሪፖርቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊነትም ይከታተላል፡

10.10 በኦዲት ሪፖርቱ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ጊዜውን ጠብቆ ሲያቀርብ ቅሬታውን ይቀበላል፣

10.11 በኦዲት ሥራው ላይ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ካሉና ካላመነበት ባለሥልጣኑ ሥራውን በማስቆም በራሱ ወይም በሚወክለው ሌላ መርማሪ ማስመርመር አለበት፡፡

10.12 በተወካይ ሂሳብ መርማሪው፣ በኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እና ግለሰቦች መካከል የህግ ጥሰት ሲኖር ለህግ እንዲቀርቡ ያደርጋል፤

**አንቀጽ 11፣ የተወካይ ሂሳብ መርማሪዎችን ዝርዝር ስለመያዝ**

11.1አግባብ ያለው ባለስልጣን ውክልና የሰጣቸውን ሂሳብ መርማሪዎችን ዝርዝር ከሙሉ መረጃዎቻቸው ጋር ይይዛል፤

11.2 አግባብ ባለው ባለስልጣን የተወካይ ሂሳብ መርማሪዎችን ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

11.3 የአዲስ አበባ ኀብረት ሥራ ኤጀንሲ የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በየጊዜው በተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ዝርዝር ውስጥ የመዘገባቸውን ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎችን በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለክፍለ ከተማ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ አካላት እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ከፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ የሚላኩትን በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

11.4 የኀብረት ሥራ ማኀበራትን ሂሣብ በውክልና ለመመርመር የሚፈልጉ ሂሳብ መርማሪዎች አግባብ ያለው ባለስልጣን ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ከሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ጋር ማመልከቻቸውን አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

11.5 አግባብ ያለው ባለስልጣን የምዝገባ ጥያቄውን መርምሮ መስፈርቱን ለሚያማሉ አመልካቾች መመዝገባቸውን የሚገልጽ ማስረጃ በአንድ ቀን ውስጥ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 12፣ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎችን ስለመምረጥ፣ ስለመመደብና ስለማንሳት

12.1 ኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት ተወካይ ሂሳብ መርማሪ መምረጥ የሚችሉት አግባብ ያለው ባለስልጣን መዝግቦ የያዛቸውን ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ብቻ ነው፡፡

12.2 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ የኦዲት ተደራጊውን ኀብረት ሥራ ማኀበር ሂሣብ ለመመርመር የሚያሰማራቸውን ባለሙያዎች ዝርዝር መረጃ /ፕሮፋይል/ አግባብ ላለው ባለሥልጣን በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡

12.3 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ አግባብ ላለው ባለሥልጣን አሳውቆ ያሰማራቸውን ሂሳብ መርማሪዎች ሲቀይር ወይም ከሥራ ላይ ሲያነሳ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማሳወቅ አለበት፣

12.4 ኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኅበር ከመረጠው ተወካይ ሂሳብ መርማሪ ጋር የገባውን የውል ስምምነት ለማቋረጥ የሚያበቃ አለመግባባት ሲኖር ውሉን ከማቋረጡ በፊት ምክንያቶቹን በመዘርዘር አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማሳወቅ አለበት፣

12.5 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ በተከታታይ ከ2 ጊዜ በላይ አንድን ኀበረት ሥራ ማኅበር ኦዲት ሊያደርግ አይችልም፡፡

12.6 የሂሳብ ምርመራው ቡድን አባላት ቢያንስ ከ 2 ያላነሱ አባላት ያሉት መሆን አለበት፡፡

# ክፍል ሦስት

## ለሂሳብ ምርመራው ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና ሌሎች ተግባራት

### አንቀጽ 13፣ በኦዲት ተደራጊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት መደረግ ስለሚገባው ቅድመ ዝግጅት

13.1 ሂሣባቸውን በተወካይ ሂሳብ መርማሪ የሚያስመረምሩ ኀብረት ሥራ ማኅበራት ለዚሁ ሥራ የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍን በጀት አስቀድመው መያዝ አለባቸው፡፡ ስለ በጀቱ የኀብረት ሥራ ማኀበራቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይወስናል፣

13.2 ኀብረት ሥራ ማኀበራት ሂሣባቸውን በተወካይ ሂሳብ መርማሪ ለማስመርመር አግባብ ላለው ባለሥልጣን የጽሁፍ ጥያቄ በማቅረብ ፈቃድ ያገኙበትን ማስረጃ መያዝ አለባቸው፣

13.3 ኀብረት ሥራ ማኀበራት አግባብ ያለው ባለስልጣን የመዘገባቸውን ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎችን በግልጽ ጨረታ አወዳድረው የውል ስምምነት መፈጸም አለባቸው:: ውሉንም አግባብ ላለው ባለስልጣን በማሳወቅ ወደ ሥራ መግባት አለባቸው፡፡

13.4 በኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኅበር እና በተወካዩ ሂሳብ መርማሪ መካከል የኦዲት ሥራውን ሽፋን፣ ሥራው የሚወስደውን ጊዜ፣ የአገልግሎት ክፍያውን፣ አግባብ ያለውን የኦዲት ሥልት፣ ሠነዶችን፣ ሠራተኞችን፣ ቁሳዊ ንብረቶችን፣ በሦስተኛ ወገን ኃላፊነት ሥር ያሉትን ጭምር እና በኦዲቱ የሥራ ሂደት እንዴት ከኦዲተሮች ጋር መገናኘት እንደሚቻል የሥራ ውል መፈረም ይኖርበታል፣

13.5 ኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኅበር የሰየመውን ተወካይ ሂሳብ መርማሪ፣ ሂሳብ መርማሪው ከኦዲት ተደራጊው ኀብረት ሥራ ማኅበር ጋር የገባውን ስምምነትና ቢጋር ሥራው ከመጀመሩ በፊት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማሳወቅ አለበት፣

13.6 ኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሆኑ እና ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ማንኛውንም ዓይነት የሂሣብ ሰነዶች፣ ውሎች፣ የሂሣብ መዛግብት፣ የቃለ ጉባኤ መዝገብ፣ የአባላት መዝገብ፣ እና የመሳሰሉትን ማናቸውንም ሰነዶች እና መዛግብት አዘጋጅተው ለተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ለምርመራው ማቅረብ አለባቸው፡

13.7 ኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው የሂሳብ አያያዝ መርህ፣ የሂሣብ መግለጫዎች ሪፖርት ስታንደርድ እና አግባብ ያለው ባለሥልጣን ባወጣው የሂሳብ አያያዝ መመሪያ መሠረት ሂሣባቸውን መያዝና የሂሳብ መግለጫዎችን ማዘጋጀት አለባቸው፤

13.8 ኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለሂሳብ መርማሪዎቹ በቂ የሥራ ቦታ እና በሂሳብ ምርመራ ሥራቸው ወቅት በቅርብ መረጃ የሚሰጣቸው ባለሙያ መመደብ ይኖርባቸዋል፣

13.9 ኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተወካይ ሂሳብ መርማሪ ውል ፈጽመው ሂሳባቸውን ሲያስመረምሩ የታወቀም ሆነ ያልታወቀ የጥቅም ግጭትና የተዛባ አመለካከት ሊያመጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን አስቀድመው ማስወገድ አለባቸው፤

13.10 ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በስሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶችና የሥራ ዘርፎች ካሉ ሂሳቡን በየዘርፉና በየፕሮጀክቱ ለይቶ መዝግቦ በመያዝ የሂሳብ መግለጫ የመሥራት ግዴታ አለበት፣

## አንቀጽ 14፣ ተወካይ ሂሣብ መርማሪዎች በሥራቸው ወቅት ትኩረት ሊያደርጉባቸው ስለሚገቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጾች እና ሌሎች ነጥቦች፤

14.1 ኅብረት ሥራ ማኅበራት ከሌሎች የንግድ ተቋማት የሚለዩበት የራሳቸው የሆነ ፀባይ ስላላቸው ተወካይ ኦዲተሮች በኦዲት ሥራቸው ወቅት በተለይ የሚከተሉትን ነጥቦች ማየት አለባቸው፡፡ በዚህም መሠረት፣

14.1.1 ከማንኛውም ማኅበር ስም መጨረሻ ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚሉት ቃላት መፃፋቸውን

14.1.2 መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት ቁጥር ከአስር በታች ወይም አግባብ ያለው አደራጅ መ/ቤት ከወሰነው ቁጥር በታች አለመሆኑን ማረጋገጥ፣

14.1.3 የኅብረት ሥራ ማኅበራት በማምረት ወይም በአገልግሎት ወይም በማምረትና በአገልግሎት መስክ ሊንቀሳቀሱ ስለሚችሉ ይህም በመተዳደሪያ ደንባቸው መጽደቁን እንዲሁም የኅ/ሥራ ማኅበሩ በተቋቋመለት አላማ ብቻ ሥራውን የሚያከናውን መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ፣

14.1.4 የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ውስጥ በመደበኛ ስብሰባ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ወይም ልዩ ውሳኔዎች አዋጁ እና በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው የአፀዳደቅ ሥነ ሥርዓት መሠረት በኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት አብላጫ ድምፅ መፅደቃቸውን፣

14.1.5 ባለፉት ዓመታት በተደረገው የሒሳብ ምርመራ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የተጣራ ትርፍ 30%ለመጠባበቂያ እየተቀነሰ በኅብረት ሥራ ማኀበሩ ቁጠባ ሂሣብ መቀመጡን እና ከመጠባበቂያ የሚቀረው 70%የተጣራ ትርፍ አደላደል በኀ/ሥራ ማኀበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መወሰኑን እና ክፍፍል መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

14.1.6 ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኀበሩ አባል በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን ውስጥ ከ10 ከመቶ በላይ ድርሻ አለመያዙን፣

14.1.7 ማንኛውም አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ካስተላለፈ ዕጣውን ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ ይዞ የቆየ መሆኑን ማረጋገጥ፣

14.1.8 የካፒታል እጥረት ያጋጠመው ኅብረት ሥራ ማኀበር የኅብረት ሥራ ማኀበሩን ዕጣ አባል ላልሆነ ሰው መሸጥ እንደሚችል እና ከአባላት ውጭ የሚሸጥ ዕጣ ዝርዝር ሁኔታ በኅብረት ሥራ ማኀበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ መወሰኑን፣

14.1.9 የኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኀበር መተደደሪያ ደንብ፣ የውስጥ ደንብና ሌሎች ውሣኔዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ፣

14.1.10 ቀድሞ ሂሣብ ምርምራ ወቅት የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ፣

14.1.11 ኅብረት ሥራ ማኀበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 በተገለጸው መሠረት የተሰጣቸውን ልዩ መብቶች/የመንግሥት ድጋፎችን/ ማረጋገጥ፣

14.1.12 ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኀበር በተቋቋመበት አላማ መሰረት ለሚያንቀሳቅሰው ማንኛውም የግብይት እንቅስቃሴ ተጨማሪ የንግድ ፈቃድ ሣያስፈልገው በዕቅዱና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በተዘረዘሩት ተግባራት ላይ መሠማራቱን መመርመር፣፡

14.1.13 እያንዳንዱ ኅብረት ሥራ ማኀበር ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ የሆነ የቁጥጥር ኮሚቴ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ሌሎች ኮሚቴዎች እንዳለው፣ በኦዲት ሥራው ወቅት ማየት እና ማረጋገጥ፣

## አንቀጽ 15፣ ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ኅብረት ሥራ ማኀበራትን ሲመረምሩ ማከናወን ስለሚገባቸው ዝርዝር ተግባራት፣

ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች የኅብረት ሥራ ማኀበራትን ሂሳብ ሲመረምሩ ትኩረት ሰጥተው ማከናወን የሚገባቸው ዝርዝር ሥራዎች ከዚህ የሚከተሉትን ይሆናሉ:-

### 15.1 በሥራ አመራር ኦዲት ትኩረት የሚሰጥባቸው፣

15.1.1 የኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኀበር ጠቅላላ የሥራ እንቅስቃሴም በኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች፣ በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ፣ የውስጥ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤውና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ውሣኔ ወይም በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጐች መሠረት መከናወኑን፣

15.1.2 የኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ቀደም ብሎ በታቀደውና ጠቅላላ ጉባኤው ባፀደቀው የሥራ ዕቅድና በጀት መሠረት የተፈፀመ መሆኑን፣

15.1.3 የሠራተኛ አስተዳደር ቅጥርና ስንብት አግባብ ባላቸው የሀገሪቱ ሕጐችና ደንቦች እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና ውስጠ ደንብ መሠረት መካሄዳቸውን፣

15.1.4 ኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር በተቋቋመበት ዓላማ መሠረት ሥራውን የፈፀመ መሆኑንና ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የተዘረዘሩት ተግባራት በአግባቡ የተከናወኑ መሆናቸውን

1.1.5 የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራዎች የማስተዳደር እና የመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት የተሰጣቸውን ኃላፊነት በኅብረት ሥራ ማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውሎች፣ በጠቅላላ ጉባኤና በሥራ አመራር ኮሚቴዎች በቃለ ጉባኤ ውሣኔዎችና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጐችና ደንቦች መሠረት ማከናወናቸውንና የመሳሰሉትን ማረጋገጥ አለበት፡፡

15.2 <u>በፋይናንስ ኦዲት ትኩረት የሚሰጥባቸው፣</u>

ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የፋይናንስ ደህንነት ለማረጋገጥ እና ኅብረት ሥራ ማኅበራት በሌሎች አካላት ዘንድ አመኔታ ለማሳደር እንዲችሉ በሂሣብ መግለጫዎች በተለይም:-

15.2.1 በሀብት እና ዕዳ መግለጫ ወይም በልዩ ሁኔታ በሚዘጋጀው የተጣራ ሃብት መግለጫ ውስ የተካተቱ ሀብቶች፡ ግዴታዎች ወይም ዕዳዎችና የተጣራው ሀብት በሀብትና ዕዳው መግለጫው ቀን በትክክል ያሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

15.2.2 በትርፍና ኪሣራ መግለጫ ውስጥ የተካተቱ የገቢና የወጪ ሂሣቦች ኦዲት በሚደረግበት የሂሣብ ዓመት ውስጥ በትክክል የተከሰቱ ልውውጦች መሆናቸውን አንድ በአንድ መመርመር፣

15.2.3 ኦዲት በሚደረግበት የሂሣብ ዓመት ውስጥ የተከናወኑ ማንኛውም የሂሣብ ልውውጦች በሙሉ በሂሣብ መግለጫዎች ውስጥ መካተታቸውን መመርመር፣

15.2.4 በኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሀብትና ዕዳ መግለጫ ወይም በልዩ ሁኔታ በሚዘጋጀው የተጣራ ሀብት መግለጫ ውስጥ የተካተቱት ሀብቶች በትክክል የኅብረት ሥራ ማህበሩ መሆናቸውን እና በግዴታ ወይም በዕዳ ውስጥ የተካተቱ ደግሞ በትክክል የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዕዳዎች ወይም ግዴታዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

15.2.5 በኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕዳ መግለጫ ውስጥ እና በትርፍና ኪሣራ መግለጫ ውስጥ

የተካተቱ ሀብቶች፣ ዕዳዎች፣ የተጣራ ሀብቶች፣ ገቢና ወጪዎች በተገቢው ዋጋቸው የተቀመጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

15.2.6 ሂሣብ ዓመቱ መዝጊያ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ የተከናወኑ የሂሣብ ልውውጦች በተገቢው የሂሣብ ዓመት ውስጥ መያዛቸውን ማረጋገጥ፣

15.2.7 በሀብት ስሌት ውስጥ የተካተቱት ተሰብሳቢ ሂሣቦች ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ሊሰበሰቡ የማይችሉ መሆን ያለመሆኑን መጠቆም እና የብድር ውሎችን፣ የዋስትና ሰነዶችን መመርመር፣

15.2.8 በሀብት ስሌት ውስጥ የተካተቱት በቆጠራ የተገኙ ንብረቶች በትክክለኛ ዋጋቸው የተመዘገቡና ያልተበላሹ እንዲሁም ጊዜያቸው ያላለፈባቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

15.2.9 በሀብትና ዕዳ መግለጫ ውስጥ የተካተቱት ቋሚ ንብረቶች በእርግጥ በአካል ስለመገኘታቸው ማረጋገጥና መግለፅ፣

15.2.10 የዘመኑን የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፣

15.2.11 የኦዲት ተደራጊውን ኅብረት ሥራ ማኅበር የሂሣብ አያያዝ ስርዓት በመፈተሽ የአገልግሎት ተቀናሽ አያያዙ እና በቆጠራ የተገኙ ንብረቶች የዋጋ ተመን ዘዴ ወጥና በየዓመቱ በተከታታይነት የተሰራበት መሆኑን ማረጋገጥ፣

15.2.12 የኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር የዕዳ /ግዴታ/ ሂሣብ ውስጥ የተካተቱት የአበዳሪዎች ወይም የአቅራቢዎች ሂሣብ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ፣

15.2.13 የኦዲት ተደራጊውን ኅብረት ሥራ ማኅበር የመመዝገቢያ፣ የዕጣ (ሼር) ሂሣብ እና የአባላትን የተሳትፎ ክፍያ መመርመር፣

15.2.14 የኦዲት ተደራጊውን ኅ/ሥ/ማ/ የግዥና ሽያጭ ሂሣብ እና የመሳሰሉትን መመርመር አለበት።

### 15.3 <u>የንብረት ቁጥጥር ኦዲት ትኩረት የሚሰጥባቸው፣</u>

ተወካይ ኦዲተሩ የኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር ቋሚ፣ ጊዜያዊ እና አላቂ ንብረቶች የግዥ ሥርዓት አጠቃቀም፣ አጠባበቅ፣ የቁጥጥር ሥርዓት እና ንብረቶች በሙሉ በአግባቡ ለኅብረት ሥራ ማኅበሩ ሥራ መዋላቸውን መርምሮ ሙያዊ አስተያየት መስጠት አለበት።

**ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ በተለይ**

15.3.1 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር የሚያካሂዳቸውን የተለያዩ ሥራዎችና ፕሮጀክቶችን ለየብቻ በመመርመር የትኛው የሥራ ዘርፍ ትርፋማ ወይም አክሳሪ እንደሆነ በመለየት ሙያዊ አስተያየት መስጠት፣

15.3.2 አግባብነት ያላቸው መመዘኛዎችን በመጠቀም የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የፋይናንስ አቋም

መገምገምና አስተያየት መስጠት፣

15.3.3 የኅብረት ሥራ ማኅበሩን የበጀት አጠቃቀም፣ የዕቅድ አፈጻጸም እና አስፈላጊ የሆኑ የሂሣብ አሰራርና የውስጥ ቁጥጥር ስልቶች በአግባቡ የተዘረጉ በጥልቀት መመርመር እና ሙያዊ አስተያየት መስጠት፣

15.3.4 አጠቃላይ በኦዲት ሥራው ወቅት የታዩ የአሰራር ድክመቶችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥና በድጋሚ እንዳይፈጸሙ የማሻሻያ ሃሣቦችን ነጥብ በነጥብ ማስቀመጥ አለበት፡፡

## ክፍል አራት የኦዲት ሪፖርት

### አንቀጽ 16፣የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት አዘገጃጀት፣

16.1ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ለኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር እና አግባብ ላለው ባለሥልጣን የሚያቀርበው የኦዲት ሪፖርት የሂሣብ ሰነዶችን ወይም የአሰራር ሕጋዊነትን የሚያረጋግጡ ሪፖርቶችን ተቀባይነት ባገኙ ዓለም አቀፍ የኦዲት ስታንደርዶች መሠረት ማረጋገጥ አለበት፣

16.2 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ የኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ መይም የአሰራርን ሕጋዊነት ሲያረጋግጥ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን አዋጅ፡ ደንብ፡ መመሪያዎች እና የኅብረት ሥራን መርህ እንዲሁም የአገሪቱን ሌሎች ሕጐች መሠረት በማድረግ መሆን አለበት፣

16.3 የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲት ተደራጊው ህብረት ሥራ ማህበር የሂሣብ አያያዝና የሂሳብ መግለጫዎች አዘገጃጀት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው የሂሣብ አያያዝ መርህ እና የሂሣብ መግለጫዎች እና ሪፖርት ስታንደርድ እንዲሁም አግባብ ያለው ባለስልጣን ባወጣው መመሪያ መሠረት መከናወኑን እና በተከታታይ አመታት ወጥ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው መግለፅ ይኖርበታል፡፡

16.4 የኦዲት ሪፖርት የኦዲት ተደራጊውን ኅብረት ሥራ ማኅበር የሂሣብ መግለጫዎች አስመልክቶ የኦዲት አስተያየት የያዘ ወይም አስተያየት ለመስጠት የማይቻል ከሆነም "አስተያየት ለመስጠት አልተቻለም" የሚል ዓረፍተ ነገር ሊይዝ ይገባል፡፡

16.5 የኦዲት ሪፖርቱ ለኦዲት የመነሻ ሂሣብ ያለፈው የሂሣብ ምርመራ ሪፖርት ወይም ከዚህ ቀደም ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ ከሆነ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ የተዘጋጀው የመነሻ ሂሣቡ መሆኑን መግለፅ አለበት፡፡

### አንቀጽ 17፣ የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ስለሚቀርብበት ጊዜ

የኦዲት ሥራው ከተጠናቀቀ በኂላ የኦዲት ሪፖርቱ ከአሥራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ አግባብ ላለው ባለሥልጣን መድረስ አለበት፡፡

## አንቀጽ 18፣ ስለ ሂሳብ ምርመራ ሪፖርት አቀራረብ

18.1ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር በውሉ ውስጥ በመረጠው ቋንቋ የኦዲት ሪፖርቱን በበቂ ኮፒዎች አዘጋጅቶ በአንቀጽ 17 በተወሰነው ጊዜና ቀን አግባብ ላለው ባለሥልጣን ወይም ለወከለው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ መ/ቤት ማቅረብ አለበት፣

18.2 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ኦዲት ሪፖርቱ ለጠቅላላ ጉባኤ በሚቀርብበት ቀን በጉባኤው ላይ በመገኘት ኦዲት ሪፖርቱን በተመለከተ ብቻ  በጉባኤ አባላት ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡

## አንቀጽ 19፣ የሂሳብ መግለጫዎችና አባሪዎች

ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ከኦዲት ሪፖርቱ ጋር የሚከተሉትን በአባሪነት ማቅረብ አለበት፡፡

19.1የሀብት እና ዕዳ መግለጫ፣

19.2የትርፍ እና ኪሣራ መግለጫ፣

19.3የተጣራ ሀብት መግለጫ፣

19.4የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ፣

19.5 አባሪ ማብራሪያዎች፣

## ክፍል አምስት  ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 20፣ ስለ ክትትልና ቁጥጥር

20.1አግባብ ያለው ባለሥልጣን ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ሥራውን በሚያከናወንበት ጊዜ ሕግን፡ የሥነ ምግባር ደንብን፣ የኅብረት ሥራ ኦዲትና አጠቃላይ የኦዲት ሙያ የሚጠይቀውን አሰራር ተከትሎ መስራቱን ያረጋግጣል፡፡

20.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) የኦዲተሩን ገለልተኛነት፣አጠቃላይ ሥነ ምግባር፣

ለ) የኦዲት ውጤቱን ተአማኒነት፣

ሐ) የኦዲተሩን አመራረጥና በኦዲተርነት የተመደቡ ባለሙያዎች ስለሚመረጡበትና ስለሚነሱበት
ሁኔታ፣

መ) ኦዲተሩ ሥራውን ያከናወነበት ስልት፣

ሠ) ኦዲተሩ ሥራውን  በሚያከናውንበት ጊዜ በዓለም አቀፍ የኦዲት ስታንደርድ መሠረት ማከናወኑን፣

ረ) ተወካይ ኦዲተሩ ሥራውን በሚየከናውንበት ወቅት የተከሰቱ አለመግባባቶች፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችንና አለመግባባቶችን  ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎችን፣

ሰ) ከኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት አመራር ኮሚቴዎች፣ ቅጥር ሠራተኞችና የሥራ መሪዎች ጋር የተደረጉ ግንኙነቶች፣

ሸ) ሌሎች ከውጭ ኦዲተር፣ ከኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበርና ከኦዲት ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

20.3 በተወካይ ኦዲተሩ ተዘጋጅቶ የቀረበውን የኦዲት ሪፖርት ለኅብረት ሥራ ማኅበሩ ቀርቦ ከመወሰኑ በፊት አግባብ ባለው ባለሥልጣን ቀርቦ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ትክክለኛነቱ ይረጋገጣል፡፡

## አንቀጽ 21፣ መረጃን ስለመግለጽ

አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወይም ኦዲት ተደራጊው ኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም አካላት በምርመራ ሂደት ወይም በማናቸውም ሁኔታ ስለተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች አሰራር፣ የሥነ ምግባር ጉድለት ወይም የሙያ ጥፋት ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን በሚያውቅበት ጊዜ አግባብ ላላቸው የመንግሥት አካላት የሙያ ፈቃድ ለሰጠው አካል፣ ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ አባል ለሆነበት የሙያ ማኅበር እና ሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 22፣ ሥልጠና ስለመስጠት

አግባብ ያለው ባለስልጣን ተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች በኅብረት ሥራ ማኅበራት ላይ ያላቸውን እውቀት ለማጎልበት እንዲችሉ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ህግ፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም የኦዲት አሰራር እና በሌሎች ተመሳሳይ ዘርፎች ላይ በየወቅቱ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ሂሣብ እንዲመረምሩ ለመዘገባቸው ሂሳብ መርማሪዎች ይሰጣል፣ ተወካይ ኦዲተሮችም በዚህ ሥልጠና የተሳተፉ መሆን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 23፣ የኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅብራት እና የኦዲት ተደራጊ አካላት ግዴታ እና ተጠያቂነት

23.1 ኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የኅብረት ሥራ ማኅበሩ የሆኑ እና ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ማንኛውም ዓይነት የሂሣብ ሰነዶች፣ ውሎች የሂሣብ መዛግብት፣ የቃለ ጉባኤ መዝገብ፣ የአባላት መዝገብ እና የመሳሰሉትን ማናቸውም ሰነዶች ለውጭ ኦዲተሩ ለምርመራ ማቅረብ አለባቸው፣

23.2 ኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራትም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው የሂሣብ አያያዝ መርህ እና የሂሣብ መግለጫዎች ሪፖርት ስታንደርድ መሠረት ሂሳባቸውን የመያዝ ግዴታ አለባቸው፣

23.3 ኦዲት ተደራጊ አካላት ለምርመራ ያቀረቧቸውን የሂሣብ ሰነዶችና መዛግብት፣ ውሎች እና ለማናቸውም ሰነዶች ትክክለኛነት ኃላፊነት አለባቸው፣

23.4ኦዲት ተደራጊ አካላት የኦዲት ሥራው ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ለምርመራው ሥራ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፣

23.5 ኦዲት ተደራጊ አካላት ለሚፈጽሟቸው ጥፋቶች ወይም በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ላይ ላደረሷቸው ጉዳቶች በወንጀል እና በፍትሐ ብሔር ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

23.6 ኦዲት ተደራጊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለሚፈጽሟቸው ጥፋቶች አግባብ ላለው የወንጀል /የፍታብሄር/ ተጠያቂ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 24፣ የተወካይ ሂሳብ መርማሪዎች ተጠያቂነት እና ኃላፊነት፣

24.1ማንኛውም ተወካይ ሂሳብ መርማሪ ሙያዊ ሥነ ምግባር በመላበስ በጥንቃቄና በትጋት ሥራውን ማከናወን ይኖርበታል፡፡

24.2 የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሂሣብ እንቅስቃሴ ብቻ ሣይሆን ኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ መርሆዎች እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት የኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት መንቀሳቀሳቸውን እና

ለተደራጅበት ዓላማ እየሰሩ መሆኑን ማጣራት ይኖርበታል፡፡ ይህንንም በብቃት ለማከናወን የኅብረት ሥራ መርሆዎችን ደንቦችን እንዲሁም ኅብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 985/2009 ማወቅ አለበት፣

24.3 ማንኛውንም ተወካይ ሂሳብ መርማሪ ሙያው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ወይም በሕግ ላይ የሰፈሩ ግዴታዎችን ሳይከተል በመቅረቱ ያረጋገጠው የሂሣብ መግለጫ ወይም የአሰራር ሕጋዊነት ማረጋገጫ ሪፖርት ላይ የሠፈሩ ነገሮች ትክክለኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ወይም የኦዲት ተደራጊውን ኅብረት ሥራ ማኅበር የፋይናንስ አቋም የማይገልፁ በመሆናቸው በማናቸውም ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ተጠያቂ ነው፣

24.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ሆን ብሎ ሀሰት የሆነ መግለጫ ከሰጠ ወይም፣ከመስከረ ወይም የሚያውቀውን የወንጀል ድርጊት መፈጸምን ለሚመለከተው አካል ከማሳወቅ ከተቆጠበ ወይም በሂሳብ ምርመራው የደረሰበትን ሃቅ ሆን ብሎ ከሸፋፈነ በፍትሐ ብሔር እና በወንጀል የሚያስከትለው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ነው፡፡

24.5 ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ላጠፋው ጥፋትና ስለተወሰደው አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሙያ ፈቃድ ለሰጠው አካል እና አግባብ ላላቸው የመንግስት አካላት ያሳውቃል፡፡

24.6_ተወካዩ ሂሳብ መርማሪ ሙሉ የሰነድ ምርመራ ማድረግ አለበት፣

24.7_ማንኛውም ተወካይ ሂሳብ መርማሪ አግባብ ካለው ባለሥልጣን ሠራተኛ ጋር በመሆን ላጠፋው ጥፋት በወንጀልም ሆነ በፍታብሔር በጋራ ከመጠየቅ አይድንም፤

24.8_በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች እያወቀ ወደ ተግባር የገባ ተወካይ ሂሳብ መርማሪ ኃላፊነቱን በራሱ ይወስዳል አግባብ ባለው ህግም ይጠየቃል፡፡

<u>**አንቀጽ 25፣ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ መመሪያ ከ መጋቢት 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ ይውላል፡፡

ውብነህ እምሩ

የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ